# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደሪያ

# ደንብ ቁጥር 13/2018

2018

አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

የሀገራችን ስፖርት በተለያዩ ጊዜያት በአደረጃጀትና በአመራር መዋቅሮች ህዝብ በቁጥር የሚያዳግቱ ውስብስብ ችግሮች ያለፈ እና የነበረ መሆኑ ይታወቃል፣ በዚህ መሰረፈት የኤ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት በስፖርቱ ዘርፍ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ለመጀመሪያ ጊዜ በ1990 ዓ.ም የስፖርት ፖሊሲ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት የፀደቀ ሲሆን ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታዊና ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች በአደረጃጀታቸው በመዋቅር ተጠናክረው የተሰጣቸውን ሚና እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በቀጥታ ስፖርቱን የሚወክሉ መንግስታዊ መዋቅሮችን ከከተማ እስከ ወረዳ ድረስ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እንዲሁም ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶችን በከተማ፣ በክ/ከተማ፣ በወረዳ ደረጃ ምክር ቤቶችን፣ ፌዴሬሽኖችን፣ አሶሴሽኖችን፣ አደራጅ ኮሚቴዎችና የስፖርት ኮሚቴዎችን በተለያዩ የስፖርት ዓይነቶች በማቋቋምና ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ሆኖም ግን መዋቅሮች በአደረጃጀታቸው የተጠናከሩ ቢሆኑም ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች **ከ1995ዓ.ም እስከ 1997ዓ.ም** ጀምሮ የተለያዩ መቋቋሚያና መተዳደሪያ መመሪያዎች ወጥቶላቸው ቢደራጁም የተጠበቀውን ውጤትና የከተማውን ህብረተሰብ የስፖርት ፍላጎት አገልግሎት በመስጠት አርክተዋል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ከ**1997 - 2003ዓ.ም** ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት በቢሮ ደረጃ የተደራጀ ሲሆን በመቀጠልም **ከህዳር 2003-ህዳር 2008ዓ.ም** ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን ደረጃ ሆኖ **ከህዳር 2008 - 2010ዓ/ም** ጀምሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ ከ2011 – 2013 ዓ/ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን በሚል መጠሪያ ሲጠቀም ቆይቶ በ2014 ዓ/ም በአዋጅ ቁጥር 74/2014 **አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ** የሚል መጠሪያ ስያሜ የተሰጠው ሲሆን በ2016 ዓ.ም የአስፈጻሚ አካላትን መልሶ ለማደራጀት በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 **አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በሚል** በአዲስ መልክ ተደራጅቷል፡፡

ይህንን ተከትሎ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት የስፖርት ማህበራትን የማቋቋምና የማደራጀት ስልጣን በተሰጠው መሰረት የከተማዋን ሕዝባዊ ስፖርት አደረጃጀት ከቀደሙት ችግሮች በመነሳት ጥራት ያለው፣ ወጥ የሆነ፣ ተጠያቂነትና ግልፅነት ያለበት እንዲሁም የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር በአሰራርና በአተገባበር ተስማሚ የሆነ የስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደርያ ደንብ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ ደንብ ተዘጋጅቷል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በአዋጅ **ቁጥር 84/2016** በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት የአዲስ አበባ ስፖርት ምክር ቤት ይህንን የስፖርት ማህበራት ፌደሬሽኖች መቋቋሚያና መተዳደርያ ደንብ አውጥቷል፡፡
3. **አጭር ርዕስ፤**
   ይህ መመሪያ **የአዲስ አበባ ስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ** ቁጥር 13/2018 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡
   3.1. **ትርጓሜ፡**

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

3.1.1. "**ስፖርት**"፦ ማለት በኢትዮጵያ ስፖርት ፖሊሲ መሰረት ማንኛውም ግለሰብ አቅሙ በፈቀደ መጠን በግሉ ወይም በጋራ በተደራጀና ባልተደራጀ መልክ የሚከናወኑ የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎች ሆኖ የስፖርት ስልጠናዎችንና ውድድሮችን ያጠቃልላል፡፡

3.1.2. "**የከተማ አስተዳደር**"፦ ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

3.1.3. "**ቢሮ**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርቱን በበላይነት እንዲመራ በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ተቋም ማለት ነው፡፡

3.1.4. "**ስፖርት ምክር ቤት**"፦ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በመተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 11/2018 የተቋቋመ ም/ቤት ነው፡፡

3.1.5. "**የስፖርት ማህበር**"፦ ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ በፌዴሬሽን፣ በአሶሴሽን፤ በአደራጅ ኮሚቴ፣ በስፖርት ኮሚቴ ደረጃ የተቋቋመና አንድን ስፖርት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው፡፡

3.1.6. "**ፌዴሬሽን**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ የተቋቋመና አንድን ስፖርት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው የስፖርት ማህበር ነው

3.1.7. "**የስፖርት አሶሴሽን**"፦ ማለት አንድ ስፖርት ለመምራትና ለማስፋፋት የፌዴሬሽንን አቅም እስኪያሟላ ድረስ የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

3.1.8. "**የስፖርት አደራጅ ኮሚቴ**" ማለት አንድ ስፖርት ለመምራትና ለማስፋፋት የአሶሴሽን አቅም እስኪያሟላ ድረስ የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

3.1.9. "**የስፖርት ኮሚቴ**" ማለት አንድ እና ከአንድ በላይ የስፖርት ዓይነቶችን በወከሉት የህብረተሰብ ክፍል ለማስፋፋት፣ ለመምራት፣ ለማስፈፀምና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

3.1.10. "**የስፖርት ክለብ**"፦ ማለት የስፖርት እንቅስቃሴን ለማራመድ በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶና በስፖርት ማህበራት ተመዝግቦ በስልጠናና በውድድር ለመሳተፍ የተቋቋመ የስፖርት ክለብ ነው፡፡

3.1.11. "**የስፖርት ቡድን**"፦ ማለት የስፖርት እንቅስቃሴን ለማራመድ በስፖርት ማህበራት ተመዝግቦ የተቋቋመ /የተደራጀ/ የስፖርት ቡድን ነው፡፡

3.1.12. “**የጤና ስፖርት ማህበር**”፦ ማለት በስፖርት እንቅስቃሴ ጤናቸውን ለመጠበቅ በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ የተቋቋመ የስፖርት ማህበር ነው፡፡

3.1.13. “**የታዳጊ ፕሮጀክት**”፦ ማለት በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ዕውቅና አግኝቶ ከታዳጊ ህጻናት ጀምሮ እንደ ስፖርት ባህርይ በዕድሜ ገደባቸው ሳይንሳዊና ዘመናዊ ስልጠና ወስደው ወደ ላቀ ደረጃ እስኪሸጋገሩ ድረስ የሚሰጥ ስልጠና ማለት ነው፡፡

3.1.14. “**የስፖርት አካዳሚ**”፦ ማለት በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ዕውቅና አግኝቶ በአንድ ማዕከል ውስጥ ለስልጠናው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በማሟላት አንድና ከአንድ በላይ በሆኑ የስፖርት ዓይነቶች ሳይንሳዊና ዘመናዊ ስልጠና የሚሰጥና ኤሊት ስፖርተኞችን የሚያፈራ ተቋም ማለት ነው፡፡

3.1.15. “**ዓቃቢ ነዋይ”፦** ማለት በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ የፌዴሬሽኑ ንብረትና ገንዘብ የሚከታተልና የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ነው፤

3.1.16. “**አባል”፦** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ አባል እንዲሆን ተቀባይነት ያገኘና በጉባኤው በድምጽና ያለድምጽ የሚሳተፍ አካል ነው፡፡

3.1.17. “**ሰው”፦** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3.1.18. “**ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ”፦** ማለት አንድን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ማህበርን ለመምራት በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥና የስፖርት ማህበሩን ሥራ በበላይነት የሚያስፈፅም አካል ነው፡፡

3.1.19. “**የስፖርት ሙያተኞች ማህበር**”፦ ማለት በስፖርቱ ዘርፍ የሙያ ማህበር የመሰረቱ እና አንድን የተወሰነ ህጋዊ ዓላማ ለማሳካት ራዕይ ያላቸው በአሰልጣኝነት፣ በዳኝነትና በአትሌትነት ሙያ ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች ስብስብ ነው፡፡

3.1.20. “**የስፖርት ጥምረት**”፦ ማለት የተለያዩ ስፖርት ማህበራት አንድ በሚያደርጋቸው ጉዳይ ላይ በጋራ ለመስራት፣ በተመሳሳይ ስፖርትና ደረጃ ላይ የሚገኙ የስፖርት ክለቦች የሚያደርጉት ስምምነት ነው፡፡

## 4. የስፖርት ማህበሩ ዓላማ፤

4.1. በአዲስ አበባ ከተማ በቀጥታ የተወከለበትን ስፖርት በህብረተሰቡ ዘንድ እንዲታወቅና እንዲስፋፋ ማድረግ፤

4.2. በወከለው የስፖርት ዓይነት የአቅም ግንባታ፣ የስፖርት ስልጠናዎችን

እንዲሰጥና ውድድሮችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በማካሄድ ተተኪ ምርጥ ስፖርተኞችን ማፍራት፣

4.3. በሚወክለው የስፖርት ዓይነት በከተማ፣ በክ/ከተማና በወረዳ ደረጃ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር የተጠናከረና ከመንግስት ድጎማ ተላቀው ቀስበቀስ ራሳቸውን የቻሉ ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶችን ማጎልበት፤

4.4. በስፖርቱ የሚወጡ ዓለም አቀፋዊ፣ ክፍለ አህጉራዊ፣ አገር አቀፍና ከተማ አቀፍ ደንቦችና መመሪያዎች በከተማ ውስጥ እንዲታወቅና እንዲሰራባቸው ማድረግ፣

**5. ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር ስለማቋቋም፤**

5.1. **አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት ፌዴሬሽን መመስረት የሚቻለው ከዚህ በታቾ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-**

5.1.1. በከተማው ስፖርቱን ለማስፋፋት በተቋቋሙበት ስፖርት ብቸኛ ዓላማ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

5.1.2. ቢያንስ በ6ና ከዛ በላይ ክፍለ ከተሞች ፌዴሬሽን መደራጀቱ ሲረጋገጥ

5.1.3. በቡድን ስፖርቶች 6ና ከዛ በላይ ክለቦች ተደራጅተው መኖራቸዉ ሲረጋገጥ ነው፤

5.1.4. በግል ስፖርቶች በክፍለ ከተማ የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

5.1.5. በአርት ስፖርቶች 6ና ከዛ በላይ የስልጠና ማዕከላት ሲኖራቸው፤

5.1.6. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተመዘገቡ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢያንስ 15 አሰልጣኞችና 15 ዳኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

5.1.7. በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱ የሚዘወተርባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በራሱ፣ በኪራይና በትውስት መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

5.1.8. የስፖርት ማህበሩን ለመቋቋም የስድስት የክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት በደብዳቤ አደረጃጀቱ መኖሩን ሲያረጋግጡ፤

5.1.9. በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ሲችል፡፡

5.1.10. የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ላይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

5.1.11. ፅህፈት ቤት በራሱ፣ በኪራይና በትውስት እንዲሁም የሰዉ ሀይል መኖሩ ሲረጋገጥ

5.2. **አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት አሶሴሽን መመስረት የሚቻለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-**

5.2.1. በከተማው ስፖርቱን ለማስፋፋት በተቋቋሙበት ስፖርት ብቸኛ ዓላማ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

5.2.2. ቢያንስ በ6ና ከዛ በላይ ክፍለ ከተሞች አሶሴሽን መደራጀቱ ሲረጋገጥ

5.2.3. በቡድን ስፖርቶች 11ና ከዛ በላይ ቡድኖች ተደራጅተው መኖራቸዉ ሲረጋገጥ ነው፤

5.2.4. በግል ስፖርቶች በክፍለ ከተማ የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

5.2.5. በአርት ስፖርቶች 6ና ከዛ በላይ የስልጠና ማዕከላት በክፍለ ከተማ ሲኖራቸው፤

5.2.6. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተመዘገቡ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢያንስ 15 አሰልጣኞችና 15 ዳኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

5.2.7. በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱ የሚዘወተርባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በራሱ፣ በኪራይና በትውስት መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

5.2.8. የስፖርት ማህበሩን ለመቋቋም የስድስት የክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት በደብዳቤ አደረጃጀቱ መኖሩን ሲያረጋግጡ፤

5.2.9. በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ሲችል፡፡

5.2.10. የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ሊይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

5.2.11. ፅህፈት ቤት በራሱ፣ በኪራይና በትውስት  እንዲሁም የሰዉ ሀይል መኖሩ ሲረጋገጥ

5.3. **አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት አደራጅ ኮሚቴ መመስረት የሚቻለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-**

5.3.1. በከተማው ስፖርቱን ለማስፋፋት በተቋቋሙበት ስፖርት ብቸኛ ዓላማ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

5.3.2. ቢያንስ በ6ና ከዛ በላይ ክፍለ ከተሞች አደራጅ ከሚቴ መደራጀቱ ሲረጋገጥ

5.3.3. በቡድን ስፖርቶች በክፍለ ከተማ  የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

5.3.4. በግል ስፖርቶች በክፍለ ከተማ  የተመዘገቡ ቢያንስ 100 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

5.3.5. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተመዘገቡ ሕጋዊ የምስክር ወረቀት ያላቸው ቢያንስ 10 አሰልጣኞችና 10 ዳኞች መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

5.3.6. በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱ የሚዘወተርባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በራሱ፣ በኪራይና በትውስት  መኖራቸው ሲረጋገጥ ፣

5.3.7. የክፍለ ከተማ ስፖርት ፅ/ቤቶች በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱን የሚመራ ኮሚቴ መቋቋሙን በፅሁፍ ሲያረጋግጡ፤

5.3.8. በኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ሲችል፡፡

5.3.9. የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ሊይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

5.3.10. ፅህፈት ቤት በራሱ፣ በኪራይና በትውስት እንዲሁም የሰዉ ሀይል መኖሩ ሲረጋገጥ

5.4. **አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት ኮሚቴ መመስረት የሚቻለው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-**

5.4.1. በከተማው ስፖርቱን ለማስፋፋት በተቋቋሙበት ስፖርት ብቸኛ ዓላማ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

5.4.2. ቢያንስ በ6ና ከዛ በላይ  ክፍለ ከተሞች ስፖርት ኮሚቴ መደራጀቱ ሲረጋገጥ

5.4.3. በቡድን ስፖርቶች 6ና ከዛ በላይ  ቡድኖች ተደራጅተው መኖራቸዉ ሲረጋገጥ ነው፤

5.4.4. በግል ስፖርቶች በክፍለ ከተማ የተመዘገቡ ቢያንስ 150 ስፖርተኞች ሲኖራቸው፤

5.4.5. በክፍለ ከተማ ደረጃ ስፖርቱ የሚዘወተርባቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በራሱ፣ በኪራይና በትውስት መኖራቸው ሲረጋገጥ፣

5.4.6. የስፖርት ማህበሩን ለመቋቋም የስድስት የክፍለ ከተማ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት በደብዳቤ አደረጃጀቱ መኖሩን ሲያረጋግጡ፤

5.4.7. በስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ ማቅረብ ሲችል፡፡

5.4.8. የሂሳብ አያያዝን ሥርዓት የዘረጋ እና ኦዲትን በስራ ላይ የሚያውል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

5.4.9. ፅህፈት ቤት በራሱ፣ በኪራይና በትውስት እንዲሁም የሰዉ ሀይል መኖሩ ሲረጋገጥ

5.5. ከተራ ቁጥር 5.1. – 5.4 በዝርዝር ያሉትን መስፈርቶች እና ይህን መስፈርት መነሻ አድርጎ የሚዘጋጀውን የአሰራር መመሪያ  ያላሟሉ የስፖርት ማህበራት ፌዴሬሽን፣ አሶሴሽንና አደራጅ ኮሚቴ ሆነው ለ4 ዓመት ያህል ብቻ አንድ የስፖርት ማህበር የሚያከናወናቸውን ተግባራት እያከናወኑ መቀጠል ይችላሉ፡፡

5.6. ከተራ ቁጥር 5.1. – 5.4 በዝርዝር ያሉትን መስፈርቶች እና ይህን መስፈርት መነሻ አድርጎ የሚዘጋጀውን የአሰራር መመሪያ ያሟሉ ህዝባዊ የስፖርት አደረጃጀቶች የከተማ የስፖርት ማህበር ሆነው እንዲሰሩ ከሚመለከተው የስራ ክፍል ህጋዊ ፈቃድ ያገኛሉ፡፡

5.7. አንድ የከተማ ስፖርት ማህበር የሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበር ዕውቅና ለማግኘት ከወጣቶችና

ስፖርት ቢሮ ህጋዊ ዕውቅና ሰርተፍኬት ማረጋገጫ ሲሰጣቸው ብቻ ነው፡፡

5.8. በክፍለ ከተማ ደረጃ ያልተቋቋሙ የስፖርት ዓይነቶች በስፖርት ኮሚቴ ተደራጅተው የተሰጣቸውን ህዝባዊ ኃላፊነት መወጣት አለባቸው፡፡

## 6. የስፖርት ማህበሩ ስልጣንና ተግባር፤

6.1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤ ከመመሪያው ጋር የማይጣረስ የስፖርት ማህበሩን ልዩ ልዩ ደንብና መመሪያዎች ያወጣል፡፡

6.2. የስፖርት ቡድኖችና ክለቦች እንዲደራጁና እንዲጠናከሩ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

6.3. ከአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ህጋዊ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የተመዘገቡ የስፖርት ክለቦችን ይመዘግባል፣ ደረጃቸውን ያወጣል፣ ያወዳድራል፣

6.4. ከስፖርት ኮሚቴ ውጭ የሚገኙ የስፖርት ማህበራት ከአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮና ከሀገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ጋር በመተባበር ልዩ ልዩ የስፖርት ኮርሶችንና ስልጠናዎችን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡ በስራ ላይ ያውላል፡፡

6.5. ስፖርቱን በሚመለከት በዓለም ዓቀፍና አገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት የፀደቁትን የአሰልጣኝነትና ዳኝነት ደረጃዎችን እንዲሁም የውድድር ህጎችንና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

6.6. ስፖርቱን በተመለከተ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ያደርጋል፡፡

6.7. ተተኪ ስፖርቶችን ለማፍራት የስልጠናና ውድድር ፕሮግራሞች እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

6.8. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ያፀደቀውን መተዳደሪያ ደንብና የውስጥ መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣

6.9. የስፖርት ቤተሰቦች የስፖርቱን ሕግና ደንብ እንዲያከብሩና ስፖርታዊ ጨዋነትን እንዲያጎለብቱ ተገቢውን ሃላፊነት ይወጣል፣

6.10. ስፖርቱን በሚመለከት በአገር አቀፍና ከተማ አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ጉባኤዎች፣ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮችና አውደ ጥናቶች ላይ ይሳተፋል፣ ውሳኔዎችንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

6.11. ከቢሮው ጋር በመተባበር የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እንዲስፋፋ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ በስፖርቱ የከተማዋና የስፖርት ማዘውተርያ ሥፍራ መረጃ ያደራጃል፤

6.12. ከቢሮው ጋር በመተባበር የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎችን በሀገር ውስጥ በብዛትና በጥራት እንዲመረቱ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር አስፈላጊውን ግንኙነት ይፈጥራል፤

6.13. ስፖርቱ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር ለማድረግ የአጭር፣ መካከለኛ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ይነድፋል፣ይተገብራል፣

6.14. ስፖርቱ ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ እንዲስፋፋና እንዲጠናከር የቴክኒክ እገዛ ብሎም ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ያደርጋል፣

6.15. ስፖርቱን በህብረተሰብ አቀፍ ፕሮግራሞች በት/ቤቶች፣ በመከላከያ ሰራዊት፣ በፖሊስ ሰራዊት፣ በፋብሪካ፣ ድርጅቶች፣ ወ.ዘ.ተ... እንዲስፋፋና እንዲታቀፍ አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ያደረጋል፣

6.16. ህዝባዊ የስፖርት ክለቦች እንዲጠናከሩና እንዲቋቋሙ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፣

6.17. ለስፖርተኞችና ለስፖርት ባለሙያዎች መብትና ጥቅምን ማስከበር ግዴታዎችንም እንዲወጡ አስፈላጊውን ሁሉ ተግባር ይፈፅማል፣

6.18. ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ጋር በመነጋገር የስልጠና፣ የጥናትና ምርምር ስራዎች እንዲሰሩ ያስተባብራል፣

6.19. ከክፍለ ከተማ ስፖርት ምክር ቤቶችና ከወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት ጋር በመተባበር ስፖርቱን የሚመሩ የስፖርት ማህበራት እንዲቋቋሙ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ኃላፊነታቸውን በአግብቡ

መወጣታቸውን ይከታተላል፣

6.20. ስፖርቱን በሚመመለከት ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ ከክፍለ ከተማ ሰፖርት ጽ/ቤቶችና ኮሚቴዎች እንዲሁም ከክልልና አገር አቀፍ የስፖርት ማህበራት ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣

6.21. በከተማ ደረጃ በሚዘጋጁ ልዩ ልዩ ከተማ አቀፍ ውድድሮች፣ ፌስቲቫሎች፣ ኩነቶችና የወዳጅነት ውድድሮች ላይ ድጋፍ ይሰጣል፣

6.22. ከቢሮው ጋር በመተባበር ከተማ አቀፍ ባህሪይ ያላቸውን የስፖርት ውድድሮች በበላይነት ይመራል፣ የአዲስ አበባን ምርጥ ቡድኖች ያዘጋጃል፣ በአገር አቀፍ የስፖርት ውድድሮች እንዲሳተፉና ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

6.23. ከተማ አቀፍ ውድድሮች በክፍለ ከተማ ደረጃ እንዲዘጋጁ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

6.24. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት ጋር በመሆን ከአቻ የአለም አቀፍ ከተሞች ጋር በውድድርና ስልጠና ግንኙነት ያደርጋል፡፡

6.25. በስፖርቱ ዘርፍ የሙያ ማህበራት እንዲደራጅና እንዲጠናከር ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣

6.26. የስፖርት ማህበሩ በሰው ኃይል በፋይናንስ፣ በማቴሪያል ራሱን ችሎ እንዲደራጅ ተገቢውን ይፈጽማል፣ ራስን ለመቻል ገቢ ያመነጫል፣

6.27. በገቢ ማመንጫ ሥራ ላይ ለመሰማራት የስፖርት ማህበራት ዝርዝር ጥናትና ዕቅድ በማዘጋጀት በጠቅላላ ጉባኤዎቻቸው አቅርበው ማስጽደቅ ይኖርባቸዋል፡፡

6.28. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበውና የሚፀድቀው የገቢ ማመንጫ ዕቅድ ማህበራት ከተቋቋሙበት ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያለውና የስፖርቱን ዓላማ የማይፃረር ሊሆን ይገባል፡፡

6.29. ስፖርቱን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የማደራጀት፣ የመተንተንና የማሰራጨት

6.30. የሚመራውን ስፖርት በሚመለከት በሚቀርቡ ማናቸውም ክሶችና አቤቱታዎች ላይ ውሳኔ የመስጠት፤

6.31. ከአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የተሰጠውን የፈቃድ የምስክር ወረቀት **በየዓመቱ** የማሳደስ፤

6.32. ስፖርት ማህበሩ የሚመራውን ስፖርት በተመለከተ ለተጫዋቾች የዝውውር እውቅና የመስጠት፣

6.33. ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ፤

6.34. በአለም አቀፍ ደረጃ የፀደቀውን እና ኢትዮጵያ የተቀበለችውን የፀረ- ዶፒንግ ኮንቬንሽን መሰረት በማድረግ የወጡ ህጎችን የማክበርና የማስከበር፤

6.35. ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲሰፍን በስፖርታዊ መርሆዎችና ሥነምግባር ዙርያ ሥልጠና መስጠት፣ ስፖርታዊ ጨዋነት ሲጣስ እርምጃ መውሰድ፤

6.36. አጠቃላይ ዓመታዊ ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለቢሮውና ለስፖርት ማህበራት ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡


## 7. አባልነት፤

7.1. የአዲስ አበባ ------ ስፖርት ማህበር የኢትዮጵያ ____________ስፖርት ማህበር አባል ይሆናል፤

7.2. የክፍለ ከተማ -------- ስፖርት ማህበር የአዲስ አበባ ከተማ __ስፖርት ማህበር አባል ይሆናል፤

## 8. ማንኛውም የስፖርት ማህበር መዋቅር፣

**የስፖርት ማህበሩ፡-**




8.1. ጠቅላላ ጉባኤ፣
8.2. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣
8.3. የኦዲት ኮሚቴ
8.4. የተለያዩ ቋሚና ጊዜያዊ ንዑሳን ኮሚቴዎች፣
8.5. በከተማ ደረጃ አንድ ፅ/ቤት ኃላፊ፣ እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ ባለሙያና ሌሎች ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡
8.6. በክ/ከተማና በወረዳ ወጣቶችና ስፖርት ፅ/ቤት የሚሰየም አንድ የስፖርት ባለሙያ እንደአስፈላጊነቱ የቴክኒክ ባለሙያና ሌሎች ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

## 9. ድምፅ በመስጠት የሚሳተፉ የስፖርት ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ አባላት፡፡

9.1. የክፍለ ከተማ ስፖርት አሶሴሽኖች፣ ኮሚቴዎች ወይም ፌዴሬሽኖች ፕሬዝዳንት ወይም ስፖርት ምክር ቤት ተወካይ
9.2. ከቢሮው እውቅና አግኝተው የተመዘገቡ እና የቀጣይ በጀት ዓመት ዕድሳት ያከናወኑ የአዲስ አበባ ክለቦች /ቡድኖች/ አንድ አንድ ድምፅ፣
9.3. አንድ የአሰልጣኞች ማህበር፣ የዳኞች ማህበር፣ የአትሌቶች /ስፖርተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ፣
9.4. የስፖርት ማህበሩ ፕሬዚዳንትና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ ነገር ግን የስራ ጊዜያቸውን ጨርሰው የስፖርት ማህበሩ አዲስ ምርጫ በሚያካሂድበት ጊዜ ድምፅ አይኖራቸውም፤

## 10. ድምፅ የማይሰጡ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት

10.1. የሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበር ፕሬዚዳንት /ተወካይ
10.2. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተወካይና የስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬት /ተወካይ
10.3. የፌዴሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ /ቴክኒክ ባለሙያ
10.4. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ለስፖርቱ አስተዋፅኦ ያደረጉ ወይም በስፖርቱ የተለያየ አመራር በመስጠት ያገለገሉ የክብር አባላት ቢበዛ አምስት
10.5. ጠቅላላ ጉባኤ የፈቀደላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ቢበዛ አምስት፣
10.6. በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ኦዲት ኮሚቴ

## 11.የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዕጩ ስለማቅረብ

11.1. እያንዳንዱ የክፍለ ከተማ ስፖርት ማህበራት ወይም የስፖርት ምክር ቤት አንድ ዕጩ ለፕሬዚዳንት ሁለት ዕጩ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላሉ፣ የፕሬዚዳንትና የስራ አስፈፃሚ ተለይቶ መቅረብ አለበት። ነገር ግን ከክፍለ ከተማውም ሆነ ከሌላ የስፖርት ማህበራት ኃላፊነታቸውን ከ3 ወር በፊት መልቀቃቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይዘው ሲቀርቡ ብቻ ይሆናል።

11.2. የተመዘገቡና ድምፅ የሚሰጡ 10 ክለቦች እንደየስፖርት ማህበራት ባህርይ ከምርጫ ዘመኑ አስቀድሞ በነበረው የተሻለ አፈጻጸም መሰረት አንድ አንድ ዕጩ ለስራ አስፈፃሚ ያቀርባሉ። ነገር ግን ከክለቡም ሆነ ከሌላ የስፖርት ማህበራት ኃላፊነታቸውን ከ3 ወር በፊት መልቀቃቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይዘው ሲቀርቡ ብቻ ይሆናል።

11.3. የስፖርት ሙያ ማህበራት አንድ አንድ ለስራ አስፈፃሚነት እጩ ማቅረብ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከክፍለ ከተማውም ሆነ ከሌላ የስፖርት ማህበራት ኃላፊነታቸውን ከ3 ወር በፊት መልቀቃቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይዘው ሲቀርቡ ብቻ ይሆናል።

11.4. የዕጩዎች አቀራረብ በፅሁፍ ማህተም የኃላፊው ፊርማ ያረፈበት ሆኖ ለስፖርት ማህበሩ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ ይኖርበታል።

11.5. የስፖርት ማህበሩ ዕጩዎቹን ህጋዊነት ካረጋገጠ በኋላ ከምርጫው 15 ቀናት በፊት ይፋ ያደርጋል፡ ሆኖም አከራካሪ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበራት ህግ መሰረት ተግባራዊ ይሆናል።

11.6. ለስራ አስፈጻሚ ከሚቀርቡ ዕጩዎች መካከል ሴቶች 50 ፐርሰንት ቢሆን ይበረታታል።

## 12. ዕጩ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ብዛትና የምርጫ ሂደት

12.1. ክፍለ ከተማዎችና የተመዘገቡና ድምፅ የሚሰጡ እንደየስፖርት ማህበራት ባህርይ ከምርጫ ዘመኑ አስቀድሞ በነበረው የተሻለ አፈጻጸም ያላቸው 10 ክለቦች ዕጩዎችን ያቀርባሉ፣

12.2. ለፕሬዚዳንት ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል አንድ በጠቅላላ ጉባኤ ባገኘው ከፍተኛ ድምጽ መሰረት ይመረጣል፤ ለስራ አስፈፃሚ ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል በጠቅላላ ጉባኤ ባገኙት ከፍተኛ ድምጽ መሰረት ስድስት/ስምንት/አስር አባላትና ሁለት ተጠባባቂ ይመረጣሉ፣

12.3. የፕሬዚዳንትም ሆነ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ ይሆናል፣

12.4. የስፖርት ማህበራት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ የሚከናወነው በአራተኛው ዓመት ከመስከረም 01 እስከ 30 ድረስ ይሆናል።

12.5. በሀገር አቀፍና በሌላ ስፖርት ማህበራት ላይ በሥራ አስፈፃሚነት ያገለገሉ ሆነው ዕጩ ሆነው ሲቀርቡ ከነበሩበት ሥፍራ ምንያህል ዘመን በስራ አስፈፃሚ እንዳገለገሉ እና ከ3 ወር በፊት መልቀቃቸውን የሚገልጽ መልቀቂያ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል።

12.6. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን ማብቂያው በየአራት ዓመቱ ስለሆነ በጉባኤው አስመራጭ ኮሚቴዎች ከ3 - 5 አባላት ያሉት ይዋቀራል።

12.7. ም/ፕሬዝዳንትና ዓቃቤ ነዋይ ከተመረጡ ስድስት/ስምንት/አስር ዕጩዎች መካከል በግልጽ ወይም በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ በጠቅላላ ጉባኤ ይሰየማሉ።

## 13.የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር፡-

13.1. በስፖርት ም/ቤት የፀደቁትን መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ የማሻሻያ ሃሳብ ያቀርባል፣

13.2. የስፖርት ማህበሩን የውስጥ መተዳደሪያ ደንቦችን ሌሎች ማስፈፀሚያ መመሪያዎች አውጥቶ ያፀድቃል ተግባራዊ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፣

13.3. የስፖርት ማህበሩን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይመርጣል፣ ይሽራል፣

13.4. ከስፖርት ማህበሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል አንድ ፕሬዝዳንት፣ አንድ ምክትል ፕሬዝዳንትና አንድ ዓቃቤ ነዋይ ይመርጣል፣

13.5. ስፖርቱ ስለሚስፋፋበት ሁኔታ ይመክራል ለስፖርት ም/ቤቱ ሀሳብ ያቀርባል፣

13.6. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰኑ ከፍተኛ ቅጣቶችንና እገዳዎችን በመመርመር እንደ አስፈላጊነቱ በከፊል ወይም አጠቃላይ ምህረት ይሰጣል፣

13.7. የስፖርት ማህበሩን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት /ስትራቴጂያዊ/ ዕቅድ መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይገመግማል፣

13.8. የስፖርት ማህበሩን ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት ያፀድቃል፣

13.9. ዓመታዊ የስፖርት ማህበሩን የኦዲት ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

13.10. አስመራጭ ኮሚቴን ይሰይማል፡፡

## 14. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የስብስባ ስነ-ስርዓት

14.1. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣

14.2. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ወይም ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ሲጠይቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

14.3. በጉባኤው ወቅት ከግማሽ በላይ ወይም $50^{+1}$ የሆነ ድምፅ የሚሰጡ አካላት ከተገኙ ምልዕተ ጉባኤ ይሆናል፣

14.4. የውስጥ መመሪዎችን ለማፀደቅ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ለመምረጥ ወዘተ.... በመሳሰሉ ጉባኤዎች ላይ 2/3 አባላት መገኘት አለባቸው፣

14.5. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምርጫ ሲደረግ የስራ ጊዜያቸውን የጨረሱ አባላት ድምፅ አይሰጡም፣

14.6. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የሚጸድቁት በግልፅ ድምፅ አሰጣጥ ሆኖ የሚለየው በድምፅ ብልጫ ነው፣

14.7. በጉባኤው ወቅት በአንድ ጉዳይ ላይ ድምፅ ለሁለት እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው የሚደግፈው ያልፋል፡፡

14.8. በ15 ቀን አንዴ ስራ አስፈጻሚዎች የሚገናኙ ሲሆን በተደጋጋሚ 3 ጊዜ ያለአግባብ የማይገኝ ስራ አስፈጻሚ ከአባልነት በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ እገዳ ተጥሎበት በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

## 15. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ጥንቅር፡-

15.1. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ አባላት ብዛት ሰባት/ ዘጠኝ/ አስራ አንድ ሆኖ የሚከተለው ጥንቅር ይኖረዋል

- አንድ ፕሬዝዳንት
- ተቀዳሚ ፕሬዘዳንት/እንደአስፈላጊነቱ/
- አንድ ምክትል ፕሬዝዳንት፣
- አንድ አቃቤ ነዋይ፣
- አራት /ስድስት/ ስምንት አባላት
- የፌዴሬሽኑ ፅ/ቤት ኃላፊ ወይም ቴክኒካል ባለሙያ ያለ ድምጽ፣

## 16. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን፤

16.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል፤

16.2. አንድ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል መመረጥና ማገልገል የሚችለው በአንድ የስፖርት ማህበር ውስጥ ብቻ ነው፣

16.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን አራት ዓመት ሆኖ የአገልግሎት ጊዜው ጳጉሜ 05/06 ላይ ይጠናቀቃል፡፡ ብቃቱና ችሎታው እንዲሁም ፈቃደኝነቱ ተጠይቆ እንደገና በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ መመረጥ የሚችል ሲሆን በማህበረሩ ጠቅላላ ጉባኤ አስፈላጊነቱ ከታመነበት ለአንድ የምርጫ ዘመን አርፎ በድጋሚ ለአንድ የምርጫ ዘመን እንዲያገለግል ዕድል ይሰጠዋል፡፡

## 17. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መምረጫ መመዘኛዎች

17.1. በዜግነት ኢትዮጵያዊ /ትውልደ ኢትዮጵያዊ/ የሆነ፣

17.2. ዕድሜው ከ 18 ዓመት በላይ የሆነ፣

17.3. የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ መሆኑ ሲረጋገጥ

17.4. ስፖርት ማህበሩን ለማገልገል ሙሉ ፈቃደኛ የሆነ፣

17.5. መልካም ስነ ምግባር ያለው፣ በጥሩ አርአያነት የሚጠቀስ ከፀረ-ስፖርት ድርጊትና ሱሶች ነፃ የሆነ፣
17.6. በህግ መብቱ ያልተገፈፈ
17.7. በሌሎች የስፖርት ማህበራት ወይም ኮሚቴዎች ስራን በማዳከም ወይም ህግና ደንብ በመጣስ ከኃላፊነቱ ያልተነሳ፣
17.8. የአእምሮ ህመምተኛ ያልሆነ
17.9. ቢቻል አለም አቀፍ ተምክሮ ያለዉ
17.10. ስፖርቱን በሀብቱ በእውቀቱና በሙያዉ ማገዝ የሚችል
17.11. ነዋሪነቱ በአዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ የሆነ ትውልደ ኢትዮጲያዊ ሆኖ በዜግነት ኢትዮጲያዊ ያልሆነ ሰዉ በፕሬዘዳንትነት ወይም በምክትል ፕሬዘዳንትነት ሊመረጥ አይችልም
17.12. የተመረጠ ማንም የስራ አስፈጻሚ አመራር ከስፖርት ማህበሩ ከ3 ወር በፊት መልቀቁን የሚያሳይ ደብዳቤ ሳያቀርብ በስራ ላይ እያለ በሌሎች ፌዴሬሽኖችና በሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ ፌዴሬሽኖች እጩ ሆኖ መቅረብ አይችልም
17.13. በአሰልጣኝነት፣ በዳኝነት፣ በክለብ ቡድን መሪነት ያሉ የስፖርት ባለሙያዎች በስራ አስፈፃሚና በንዑስ ኮሚቴነት ተመርጠው ማገልገል አይችሉም፣
17.14. በሀገር አቀፍ፣ በከተማ፣ በክፍለ ከተማና ወረዳ በመንግስት ስፖርት አደረጃጀቶች እና በስፖርት ማህበራት ሰራተኛ ከሆነ በስራ አስፈፃሚ መወዳደር አይችልም
17.15. የዶፒንግ የህግ ጥሰቶችን ያልፈጸመ ከሆነ
17.16. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል በመሆን በገዛ ፍቃዱ ከአባልነት እንዲነሳ የጠየቀ ከሆነና በማህበሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተሰጠበት ከሆነ በዚያዉ ምርጫ ዘመን በሌላ ስፖርት ማህበር የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሆኖ መመረጥ አይችልም።

## 18. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

18.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 21 የተጠቀሱትን ሁሉ ተግባራዊ ያደርጋል፣
18.2. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣
18.3. የስራ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
18.4. ዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣
18.5. ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ቋሚና ጊዜያዊ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባራቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣ የስራ ጊዜያቸውንም ይወስናል፣
18.6. ልዩ ልዩ የውስጥ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
18.7. ለስፖርት ማህበሩ አስተዳደርና አመራር ውድቀት በግልና በጋራ ተጠያቂ ይሆናል፣
18.8. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት መካከል በተለያየ ምክንያት ከተሰናበቱ በተጠባባቂነት ከተመረጡት ሁለት አባላት መካከል እንደ ድምፅ ቅደም ተከተላቸው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ወዲያውኑ መተካት ይችላል፡፡ ሆኖም በሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል፣
18.9. ከቢሮውና ከክፍለ ከተማ ስፖርት ምክር ቤት ጋር በመተባበር ስራውን ያከናውናል፣
18.10. በሚቀርቡ የውድድር ክለቦችና አቤቱታዎች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
18.11. የስፖርት ውድድሮች መግቢያ ትኬት ዋጋ ተመን ይወስናል፣
18.12. በከተማው የተዘረጋውን የታዳጊ ወጣቶች የስፖርት ስልጠና ልማት ፕሮግራም በተጠናከረ መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ በራሱም አደራጅቶ ይመራል፤
18.13. የስፖርት ማህበሩ የገቢ ምንጭ በቋሚነት እንዲያድግ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፣
18.14. የስፖርት ማህበሩ ፋይናንስና ንብረት ያስተዳድራል፣ ይፈቅዳል፣ በስፖርት ምክር ቤት ደንብና መመሪያ መሰረት በጋራ እየወሰነ በዕቅድ ለተያዙ ስራዎች እንዲውል ያደርጋል፣
18.15. በውሳኔዎች የጋራና የግል ተጠያቂነትና ኃላፊነት ይወስዳል፣
18.16. ራሳቸውን የቻሉ የስፖርት ማህበራት ሰራተኞች መቅጠርና ማሰናበት ይችላል፡፡

18.17. የክብር አባላትን በመለየት በጠቅላላ ጉባኤ ያጸድቃል

18.18. ፕሬዝዳንቱና ም/ፕሬዘዳንቱ በሌሉበት ጊዜ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መካከል አቃቤ ነዋይ የእለቱን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ይመራል፣

18.19. ከስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴነት ለመልቀቅ ጥያቄ ለሚያቀርብ ስራ አስፈጻሚ አባል በጋራ ተወያይቶ የውሳኔ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

18.20. የስፖርት ክለቦችና ሌሎች የስፖርት ማህበራት የይዘጋልኝ ጥያቄን ሲያቀርቡ ጉዳዩን በጥልቀት መርምሮ ለሚመለከተው አካል የዉሳኔ ሃሳብ ያሳውቃል፡፡

## 19.የስፖርት ማህበሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ስነ-ስርዓት፣

19.1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ በ15 ቀን አንድ ጊዜ ይደረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዚያ ባነሰ ጊዜ ሊደረግ ይችላል፣

19.2. በስብሰባው ወቅት ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፣

19.3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሚፀድቀው በድምፅ ብልጫ ነው፣

19.4. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ በአንድ ጉዳይ ላይ በድምፅ ለሁለት እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው የሚደግፈው ያልፋል፣

## 20.የስፖርት ማህበሩ ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባር፣

20.1. በማንኛውንም ስፍራ የስፖርት ማህበሩ ሕጋዊ ተጠሪ ይሆናል፣

20.2. የስፖርት ማህበሩን ገንዘብ ከፅ/ቤቱ ኃላፊ፣ ፋይናንስ ባለሙያ በጋራ በመሆን እንዲንቀሳቀስ ይወስናል፡፡ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡ የወጡ ወጪዎች በቃለጉባኤ እንዲደገፍና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

20.3. የጠቅላላ ጉባኤውንና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ስብሰባዎች ይመራል፣ ድምፁ እኩል ሲሆን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

20.4. የጠቅላላ ጉባኤውንና ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን በትክክል መከናወናቸውን ያረጋግጣል፡፡

20.5. አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከም/ፕሬዘዳንቱና ከአቃቢ ነዋዩ ወይም ከፅ/ቤት ኃላፊ ጋር ውሳኔ ሰጥቶ ጉዳዩን በሚቀጥለው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አቅርቦ ያፀድቃል፣

## 21. የም/ፕሬዘዳንቱ ስልጣንና ተግባር

21.1. ፕሬዘዳንቱ በማይገኝበት ጊዜ ሁሉ እርሱን ተክቶ ይሰራል፣

21.2. የፕሬዝዳንቱ የቅርብ ረዳት ሆኖ አስፈላጊውን ሁሉ ይፈፅማል፣

21.3. ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ወቅት የስፖርት ማህበሩን ገንዘብ ከፅ/ቤቱ ኃላፊ፣ ፋይናንስ ባለሙያ በጋራ በመሆን እንዲንቀሳቀስ ይወስናል፡፡ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡ የወጡ ወጪዎች በቃለ-ጉባኤ እንዲደገፍና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣

21.4. ፕሬዘዳንቱ በማይገኝበት ጊዜ አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም ከአቃቢ ነዋዩና ከአንድ ስራ አስፈፃሚ አባል ጋር ውሳኔ ሰጥቶ ጉዳዩን በሚቀጥለው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ላይ አቅርቦ ያፀድቃል፣

## 22. የዓቃቤ ነዋይ ስልጣንና ተግባር

22.1. የማህበሩን ፋይናንስ በደንቡ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

22.2. የስፖርት ማህበሩን ንብረት በአግባቡ ገቢና ወጪ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

22.3. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርበውን የስፖርት ማህበሩን በጀት ይገመግማል፣ ማሻሻያ ሀሳብ ያቀርባል፡፡ የስፖርት ማህበሩን በጀት አዘጋጅቶ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣

22.4. ለጠቅላላ ጉባኤ አጠቃላይ የፋይናንስ ንብረት ኦዲት ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፣

## 23. የስፖርት ማህበሩ ጽ/ቤት ኃላፊ ስልጣንና ተግባር፣

23.1. ተጠሪነቱ ለስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬት ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

23.2. የስፖርት ማህበሩን ጽ/ቤት ይመራል፣ እንዲሁም ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተግባራት ሁሉ ያከናውናል፣

23.3. የስፖርት ማህበሩን የአስተዳደርና የፋይናንስ ንብረት እንዲሁም የቴክኒክ ተግባሮች ይከታተላል፣
23.4. ከፕሬዝዳንቱ ወይም ም/ፕሬዝዳንቱ፣ ከፋይናንስ ባለሙያ ጋር በመሆን በስራ አስፈፃሚው ውሳኔ መሰረት የስፖርት ማህበሩን ገንዘብ ያንቀሳቅሳል፣ በቼክ ላይም ይፈርማል፣
23.5. የስፖርት ማህበሩን የፋይናንስ ንብረት በስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት መንቀሳቀሱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
23.6. የስፖርት ማህበሩ የአገር ውስጥና የአቻ ከተሞች ግንኙነቶችና የጽሁፍ ልውውጦች በፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ያከናውናል፣
23.7. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴንና የንዑሳን ኮሚቴዎችን ውሳኔ ተግባራዊ ያደርጋል፣
23.8. የስፖርት ማህበሩን ጉባኤውንና የስብሰባ አጀንዳዎችን ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመሆን ያዘጋጃል፣ የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ ቃለ-ጉባኤዎችና ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣
23.9. የስፖርት ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በደንብና መመሪያ መሰረት መከናወናቸውን ይከታተላል፣
23.10. በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ዓመታዊ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የስራ አስፈፃሚ ሪፖርት ለስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬትና ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣
23.11. የድጋፍ ጥያቄዎችን፣ የፋይናንስ ጉዳዮች በስራ አስፈፃሚ እውቅና ብቻ ይፈፀማል፣
23.12. የስራ ዘመናቸውን ላጠናቀቁ የስራ አስፈጻሚ አካላትና የንኡሳን ኮሚቴዎች የዕውቅና እና የምስጋና ፕሮግራም ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ በማጸደቅ ተግባር ላይ ያውላል፡፡

## 24. የስፖርት ማህበሩ ቴክኒካል ባለሙያ ስልጣንና ተግባር፣

24.1. ተጠሪነቱ ለስፖርት ማህበሩ ፅ/ቤት ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
24.2. የስፖርት ማህበሩን የቴክኒክ ኮሚቴ በፀሀፊነት ይመራል
24.3. የስፖርት ማህበሩን የቴክኒክ ተግባሮች ይከታተላል፣
24.4. የስፖርት ማህበሩ ችግሮችን በመለየት የጥናት ኮሚቴን በማዋቀር በስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ችግር ፈቺ ጥናት ያከናውናል፣
24.5. የስፖርት ማህበሩን የውድድርና የስልጠና መረጃዎች በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፣
24.6. በስፖርት ማህበሩ፣ በከተማ ደረጃና በስፖርት ማዕከላት የተቋቋሙ የታዳጊ ወጣቶች የስፖርት ስልጠና ፕሮግራምን ኮሚቴ እንዲደራጅ በማድረግ ይከታተላል፣ ቴክኒካል አፈፃፀሙን ይገመግማል፤
24.7. ከስፖርት ማህበሩ ፅ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡትን ተግባራት ሁሉ ያከናውናል፣

## 25. የፋይናንስ ባለሙያ ስልጣንና ተግባር

25.1. የማህበሩን ፋይናንስ በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
25.2. የስፖርት ማህበሩን ሂሳብ በአግባቡ ገቢና ወጪ ሰነዶች ይይዛል፣ ያደራጃል፣ በተጨማሪም ቼክ ያዘጋጃል፣ በቼክ ላይም ይፈርማል፣
25.3. ለጠቅላላ ጉባኤ የሚቀርብ አጠቃላይ የፋይናንስ ሪፖርትና የበጀት ዕቅድ ለዓቃቤ ነዋይ ይሰጣል፣

## 26. ስለ ንዑሳን ኮሚቴ መቋቋምና የስራ ዘመን

26.1. የስፖርት ማህበሩ ተግባርና ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ቋሚና ጊዜያዊ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣
26.2. የንዑሳን ኮሚቴ የስራ ዘመን አራት ዓመት ሆኖ የአገልግሎት ጊዜው ጳጉሜ 05/06 ይጠናቀቃል፡፡ ብቃቱና ችሎታው እንዲሁም ፈቃደኝነቱ ተጠይቆ እንደገና በድጋሚ ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ መመረጥ ይችላል፡፡
26.3. ንዑሳን ኮሚቴዎች የስራ ዘመን በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች የስራ ዘመን ይሆናል፣
26.4. የንዑሳን ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች እንደ አስፈላጊነቱ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አካላት መካከል ይሆናሉ፣
26.5. የንዑሳን ኮሚቴ አባላት ብዛት እንደ ስራ እንቅስቃሴው ከ3 - 5 ድረስ ሊሆን ይችላል፣
26.6. አንድ የንዑስ ኮሚቴ አባል መመረጥና ማገልገል የሚችለው በአንድ የስፖርት ማህበር ውስጥ ብቻ ነው፡፡

## 27. አባልነት

27.1. የስፖርት ማህበሩ የክፍለ ከተማ የስፖርት ማህበራትንና የስፖርት ክለቦችን አባል አድርጎ ይመዘግባል፡፡

## 28. የአባላት መብትና ግዴታ

28.1. የስፖርት ማህበሩ መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብን፣ የውስጥ መመሪያዎችን እና የሌሎችን የስፖርት ማህበራት የሚመራባቸውን የስፖርት ህግና ደንቦች ማክበርና መፈፀም፣

28.2. የስፖርት ማህበሩ በሚያዘጋጃቸው ከተማ አቀፍ ማንኛውንም ኩነቶችና ፌስቲቫሎች፣ ውድድሮችና ስልጠናዎች መሳተፍ፣

28.3. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የመምረጥና የመመረጥ መብት ማግኘት፣

28.4. የከተማው ስፖርት ማህበር ስፖርቱን ለማሳደግና ለማስፋፋት በሚያደረገው የልማት እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ፣

## 29. የፋይናንስና ንብረት አጠቃቀም፤

29.1. ስፖርት ማህበሩ የራሱ ባንክ አካውንት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ሁኔታዎች ተሟልተው የራሱ አካውንት እስኪኖረው ድረስ ሂሳቡ በስፖርት ም/ቤቱ አካውንት በአደራ ይቀመጣል፣

29.2. የራሳቸው የባንክ አካውንት ያላቸው የስፖርት ማህበራት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በሚወስነው መሰረት ገንዘብ በስፖርት ማህበሩ ፕሬዝዳንት ወይም ም/ፕሬዝዳንት እና ፅ/ቤት ኃላፊ የተረጋገጠና ያፀደቀው አካል ፈርሞበት በስፖርት ም/ቤቱ በተመደቡ ወይም በማህበሩ በተቀጠሩ ፋይናንስ ባለሙያዎች ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ያደርጋል፣

29.3. ለስፖርት ማህበሩ እንቅስቃሴ ከስፖርት ም/ቤቱ የሚሰጠው የበጀት ድጋፍ ድጎማ እንዲሁም ማናቸውም በድጋፍ የሚገኙ ገቢዎች በስፖርት ማህበሩ የባንክ ሂሳብ ወይም በስፖርት ም/ቤት አካውንት ገቢ መደረግ አለበት፣

29.4. ማንኛውም ገንዘብና ንብረት ገቢ ወጪ የሚሆነው ስፖርት ም/ቤቱ ባሳተመው የፋይናንስ ንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች ብቻ ሲሆን እያንዳንዱ የስፖርት ማህበር ስፖርት ም/ቤቱ የሚያሳትመውን ደረሰኝ ከቢሮው በግዢ መውሰድ ወይም ቢሮው ሲፈቅድ የራሱን ገቢ ወጪ ደረሰኝ ማሳተም ይኖርበታል፣

29.5. ለጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን /ፒቲ ካሽ/ በስፖርት ምክር ቤቱ ደንብ መሰረት በተመደበላቸው የፋይናንስ ባለሙያ እጅ ይቀመጣል፣

29.6. በቢሮው የተመደበው የፋይናንስ ባለሙያ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰነውን ፒቲ ካሽ በስፖርት ም/ቤቱ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ያንቀሳቅሳል፡፡

29.7. የስፖርት ማህበሩ ፅ/ቤት ኃላፊ በስፖርት ም/ቤቱ የተወሰነውን ፒቲ ካሽ በፋይናንስ መመሪያ መሰረት ይመራል፣

29.8. የስፖርት ማህበሩ ፅ/ቤት ኃላፊ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተወሰነውን ንብረት፣ በስጦታ የተሰጠም ሆነ በግዢ የተፈፀመ በስፖርት ምክር ቤት የፋይናንስና ንብረት መመሪያ መሰረት ገቢ ወጪ ሆኖ ያንቀሳቀሳል፣

29.9. የስፖርት ማህበሩ ንብረት ከመንግስት በተመደበው የማህበሩ ፅ/ቤት ኃላፊ ወይም ህጋዊ ቅጥር በተፈፀመለትና በቂ ዋስ ባለው ሰራተኛ እጅ ብቻ ርክክቡ ይፈፀማል፤

29.10. ራሳቸውን ያልቻሉ የስፖርት ማህበራት ሙሉ ለሙሉ ራሳቸውን ችለው እስኪወጡ ድረስ የፋይናንስ ባለሙያ በቢሮው ይመደባል፣

29.11. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የስፖርት ማህበሩ ገንዘብ አሰባሰብና አወጣጥ በአብዛኛው ቅድሚያ ሊሰጣቸው ለሚገባ የልማት እቅዶች እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

29.12. ለተለያዩ ጉዳዩች ወጪ የሆነ የስፖርት ማህበሩ ገንዘብ ስራው ባለቀ ቢበዛ በ7 ቀናቶች ውስጥ ማወራረድ አለበት፣

29.13. የስፖርት ማህበሩ በስፖርት ምክር ቤቱ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ስራውን ተግባራዊ ያደርጋል፣

## 30. ስለ ሂሳብ ምርመራ

30.1. የስፖርት ማህበሩ ሂሳብ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ወይም ስፖርት ም/ቤቱ በሰየማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ እየተመረመረ በስፖርት ማህበሩ ለጠ/ጉባኤ ይቀርባል አጠቃላይ የኦዲት ሪፖርቱ ለስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክቶሬት ብቻ በጽሁፍ ይቀርባል፡፡

## 31. ራስን በራስ ማስተዳደር ስለመቻል

31.1. አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር ራስ በራስ የማስተዳደር መብት አለው፣

31.2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ድንጋጌ ቢኖረውም አንድ ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር ራስን በራስ ማስተዳደር የሚችለው፡-

- የራሱ የሆነ ፅ/ቤት ሲኖረው ወይም በኪራይ ወይም በስጦታ መሆኑን ማረጋገጫ የሚያመጣ፣
- የሚጠቀምበት የራሱ የሆነ ካርታ ያለው ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ካልሆነም በትውስት፣ በኪራይ ሲኖረው
- ቋሚ የገቢ ምንጭ ሊኖረው ይገባል፣
- ስፖርት ማህበሩ አስፈላጊ የሰው ኃይል ማሟላት ሲችል

31.3. ራሱን ለማስተዳደር ጥያቄ ያቀረበው የስፖርት ማህበር ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች በበቂ ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ በወጣቶችና ስፖርት ቢሮና የከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት ራሱን እንዲያስተዳድር ሊፈቅድለት ይችላል፣

31.4. የስፖርት ማህበሩ ራሱን እንዲያስተዳድር በተፈቀደለት ጊዜ የስፖርት ም/ቤቱ የፌደራልና የከተማ አስተዳደሩን የስፖርት ፖሊሲ ህጎች፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አክብሮ መስራቱን በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ድጋፍና ክትትል ይደረግለታል፣

## 32. የተከለከለ ተግባር

32.1. ማንኛውም የስፖርት ማህበር በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በጎሳና በዘር መደራጀት፣ ስያሜና አርማ በተመሳሳይ በዚህ ሁኔታ የተደራጁትን ክለቦችን ተቀብሎ ዕውቅና መስጠት አይችልም፣

32.2. የስፖርት ማህበሩ አባል በተለያዩ ጉዳዮች የወሰዱትን ገንዘብ ሳያወራርዱ ሌላ ገንዘብ በስማቸው ወጭ አድርጎ መስጠት አይቻልም፣

32.3. የስፖርት ማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ በግል ማህበራዊ ሚዲያ፣ ፖ.ሣ.ቁ.፣ ፋክስና ኢሜል አድራሻ መጠቀም አይችልም፡፡ የስፖርት ማህበሩ የራሱ የመልዕክት አድራሻ ከሌለው በቢሮው የመልዕክት አድራሻ መጠቀም ይኖርበታል፣

32.4. አንድ ሰው በስራ አስፈፃሚ ወይም በቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴ አባልነት ሊያገለግል የሚችለው በአንድ የስፖርት ዓይነት በአንድ ክለብ ወይም ከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር ብቻ ነው፣

32.5. በየደረጃው የሚገኙ የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ የክፍለ ከተማና የወረዳ ስፖርት ዘርፍ ቋሚ ሰራተኞች የስፖርት ማህበር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሆነው መመረጥ አይችሉም፣

32.6. የስፖርት ክለቦችን በመወከል በከተማ አቀፍ የስፖርት ማህበር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ንዑሳን ኮሚቴ አባል ሆኖ የተመረጠ የክለብ አመራር በራሱ ክለብ አባል ሆኖ መቀጠል አይችልም፣

32.7. ማንኛውም ስፖርት ማህበር ምንም አይነት ምዝገባ ሳያደርግና ዕውቅና ሳይሰጠው መንቀሳቀስ አይችልም፣

32.8. በግልም ሆነ በቡድን በማንኛውም የስፖርት ዘርፍ ወይም በማህበርና በድርጅት ተደራጅተው መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎችና ህጎች እንዲሁም ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች መጣስ ወይም ለመተግበር ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት የተከለከለ ነው፡፡

32.9. በስፖርት ማህበር አሰራር ውስጥ አንድ ሰው ገንዘብ ወይንም ንብረት ራሱ ጠያቂ ራሱ አፅዳቂ በመሆን ገንዘብና ንብረት ማንቀሳቀስ አይችልም፡፡

32.10. እድሳት ሳያደርጉ የትኛዉንም ስፖርታዊ ፕሮግራም ማከናወንና መሳተፍ አይችልም፡፡

32.11. የጸረ አበረታች ቅመሞች ድንጋጌዎችን መጣስ የለበትም፣

32.12. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የሚጻረሩ ተግባራት መፈጸም አይችልም፣

32.13. ይህን ደንብ የሚጻረሩ ደንብ ማዉጣት አይፈቀድለትም፣

32.14. በማንኛዉም የስፖርት ማህበር አንድ ሰዉ ሁለት ቦታ አመራር ሆኖ መምራት አይችልም

32.15. የክለብ ቡድን መሪና የክለብ ባለቤት በተመሳሳይ ስፖርት አይነት ተመርጠዉ ማገልገል አይችሉም

32.16. ማንኛውም የስፖርት ፌስቲቫል፣ ኩነት፣ ውድድር፣ ስልጠናና ማማከር አገልግሎት ለመስጠት ከቢሮውና ከስፖርት ማህበራት ዕውቅናና ፍቃድ ውጭ ማከናወን አይቻልም።

32.17. አንድ የስፖርት ማህበር ደንቦችና መመሪያዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በጠቅላላ ጉባኤ ጸድቆ ተግባራዊ ከመደረጉ ከ15 ቀናት በፊት ለስፖርት ማህበራት ማደራጃና ውድድር ዳይሬክተር ቀርቦ ሲተችና ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው።

32.18. ከላይ በዝርዝር የተገለጹትን የተከለከሉ ተግባራት ፈጽሞ የተገኘ በህግ ተጠያቂ ይደረጋል።

## 33. የመተባበር ግዴታ:-

33.1. የተለያዩ ችግሮች ሲከሰቱና በስፖርት ማህበራት መካከል ለሚነሳው ክርክር ምክንያት ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ወይም የአስተዳደሩ ስፖርት ም/ቤት ሠነዶችንና ዶክመንቶችን ማስመርመር ሲፈልግ ማህበሩ የመተባበር ግዴታ አለበት፣

33.2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚያካሂደው የህብረተሰብ ተሳትፎና የበጎፍቃደኛ ተግባራት ላይ በንቃት መሳተፍ መቻል ይኖርበታል።

33.3. ማንኛውም አባል የስፖርት ማህበሩን በመወከል በአገር አቀፍ ስብሰባዎች ከተሳተፉ በኋላ በማህበሩ ስም የተላኩትን ሰነዶችና ዶክመንቶች እጅግ ቢዘገይ በሰባት ቀናት ውስጥ ለማህበሩ ፅ/ቤት የማስረከብ ግዴታ አለበት፣

## 34. ፆታን በተመለከተ

⇒ በዚህ መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለፀ በሙሉ ሴቶችንም ያጠቃልላል።

## 35. ኃላፊነትን ስለ አለመወጣት፤

35.1. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ኃላፊነቱን በሚገባ ሳይወጣ ሲቀር የስፖርት ምክር ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጉዳዩን አጣርቶ ወዲያውኑ ጠቅላላ ጉባኤ አስጠርቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

## 36. ቅጣት

⇒ ይህንን ደንብ የጣሰ ወይም የዚህን ደንብ አፈፃፀም ያሰናከለ ማንኛውም ግለሰብ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጣል። የስፖርት ማህበሩም የስነ-ስርዓት እርምጃ መውሰድ ይችላል።

⇒ የዚህን ደንብ ቁጥር **32** ላይ የተዘረዘሩትን የተላለፈ ማንኛውም የከተማ ስፖርት ማህበር:-

ሀ. በመጀመሪያ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ይሰጠዋል፣

ለ. በ "ሀ" በተገለፀው መሰረት ካልታረሙ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ተጠርቶ ውሳኔ እንዲተላለፍ ይደረጋል፣

ሐ. በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ካልታረሙ የስፖርት ማህበሩ ከእንቅስቃሴ ታግዶ ሌላ ምርጫ ይካሄዳል፣

መ. ማንኛውም የስፖርት ማህበራት የሚያወጡት ደንቦች ወይም መመሪያዎች ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ሆኖ ከተገኙ ቢሮዉ ወዲያውኑ የሚቃረነውን የህግ ድንጋጌ እንዲስተካከል በጽሑፍ ያሳውቃል፣ ማህበሩ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ተቀብሎ ካላስተካከለ ቢሮዉ ደንቡ ወይም መመሪያው ስራ ላይ እንዳይውል ያግዳል

## 37. ስለማሻሻል፤

⇒ ይህንን ደንብ እንዲሻሻል ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል በም/ቤቱ ጉባኤ ላይ ጥያቄ ሲቀርብ እና ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ለስፖርት ም/ቤቱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጥያቄ ቀርቦ ሲታመንበት ለጉባኤው ቀርቦ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት **2/3ኛው** ሲስማማበት ሊሻሻል ይችላል። በስፖርት ም/ቤት ጠ/ጉባዔ ሲፀድቅም ተግባራዊ ይሆናል።

## 38. ስለስፖርት ማህበራት ምዝገባና ዕውቅና ማግኘት

38.1 ማንኛዉም የስፖርት ማህበር በዚህ ደንብ የተቀመጡ መስፈርቶችን በማሟላት ደንቡ በወጣ ሶስት ወራት ጊዜ ዉስጥ ዳግም ምዝገባና የዕውቅና ሰርተፍኬት ማግኘት አለባቸዉ

38.2 በከተማ አቀፍ ደረጃ ከዚህ በፊት ያልተመዘገቡና እውቅና ያላገኙ የስፖርት ማህበር በዚህ ደንብ ዉስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች አሟልተው ሲገኙ ፍቃድ ይሰጣቸዋል

38.3 ቀደም ሲል በከተማ አቀፍ ደረጃ ተደራጅተዉ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ የስፖርት ማህበራት የተቀመጡትን መስፈርት አሟልተዉ ካልተገኙና የተሰጣቸው የአራት አመት የማደራጀት ጊዜ ከተጠናቀቀ አዲስ አበባ ከተማ አቀፍ የሚለውን ስያሜ በመተው በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

38.4. ማንኛውም የስፖርት ማህበራት ዳግም ምዝገባ ሲቀርብ በስሩ የተደራጁ ክለቦች ስያሜ፣ አርማና፣ መዝሙራቸው ከብሔር፣ ከፖለቲካና ከሃይማኖት ነፃ አድርገው መቅረብ አለባቸው፡፡

38.5 የስፖርት አሶሴሽኖች የፌዴሬሽን መስፈርት ሲያሟሉ የቀድሞ ስማቸውን ይዘው በፌዴሬሽን ደረጃ አድገው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

## 39. የፍቃድ ዕድሳት

39.1. ማንኛውም ከተማ አቀፍ ስፖርት ማህበር የፍቃድ ምስክር ወረቀት በየአራት ዓመቱ ለቢሮዉ አቅርቦ ማሳደስ አለበት፡፡

39.2. ማንኛውም ከተማ አቀፍ ስፖርት ማህበር ዕድሳት ለማድረግ የማህበሩን የፋይናንስ ሪፖርት፣ ኦዲት ሪፖርት፣ የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ዝርዝርና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ለቢሮዉ ማቅረብ ይጠበቅበታል

39.3. በተሰጠው አራት ዓመት የማደራጃ ጊዜ የሚጠበቅበትን መስፈርት ማህበሩ ካላሟላ አዲስ አበባ ከተማ አቀፍ የሚለውን ስያሜ በመተው በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

39.4. በዚህ አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 39.2 እና በፍቃድ አሰጣጥ ማስተግበሪያ ማኑዋል የተጠቀሱትን መረጃዎች አሟልቶ ያልተገኘ የስፖርት ማህበር እድሳት አይደረግለትም፡፡

## 40. ስለ መፍረስ

**40.1** የስፖርት ማህበር በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊፈርስ ይችላል፡፡

ሀ. የሥፖርት ማህበሩ እንዲፈርስ ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል 2/3ኛው ሲወስን

ለ፣ በህግ እንዲፈርስ ሲወሰን

40.2 የስፖርት ማህበሩ በዚህ ንዑስ አንቀጽ 40.1 መሰረት ከፈረሰ የማህበሩ ጠቅላ ሀብትና ንብረት ቢሮው ተረክቦ ተመሳሳይ ዓላማ ላላቸው ስፖርት ማህበራት ሊያውል ይችላል፡፡

## 41. የተሻረ ደንብ

⇒ በ2015ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የወጣው የስፖርት ማህበራት መቋቋሚያና መተዳደርያ ደንብ በዚህ ደንብ ተሸሯል፡፡

## 42. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ፤

ይህ መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ም/ቤት ----/---/-----ዓ/ም ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ወ/ሮ አዳነች አበቤ

የአዲስ አበባ ስፖርት ምክር ቤት ሰብሳቢ